ዲጼምበር - ያኑዓር 2021 ዓ.ም

# እንክብካቤ ለሚያቀርቡ ለሕመምተኛ ቤተሰቦችና ሞግዚት ሠራተኞች የተሰጡ መረጃዎች ፤

# የተጣሉት የገደብ ቀኖች



አደገኛ ደረጃ ላይ ላሉና በጣም ውድ የሆኑ የሕመምተኛ ቤተሰቦችና ለሞግዚቶቻቸው ፤ በተጣለው ገደብ የተለያዩና ልዩ የሆኑ ሁኔታዎች እያጋጠሙን እንገኛለን ፤

ውድ የሆኑ ቤተሰቦቻቸውን ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታና ጤናቸውን በመጠበቅ እንክብካቤ ለማድረግ ሲባል ፤ ከዚህ በታች በጣም ብዙና የተለመዱ ጥያቄዎችና መልሶች ይቀርባሉ ፤

המשרד לשוויון חברתי | משרד הבריאות לחיים בריאים יותר | משרד ראש הממשלה Prime Minister's Office | משרד העבודה הרווחה והשירותים החברתיים חוסן חברתי לישראל | משרד המשפטים MINISTRY OF JUSTICE | وزارة العدل

המוסד לביטוח לאומי | רשות האוכלוסין וההגירה Population & Immigration Authority سلطة السكان والهجرة | ג'וינט ישראל אשל יחד בעשייה חברתית למען הזקנים | מאיירס-ג'וינט-ברוקדייל MYERS-JDC-BROOKDALE مايرس-جوينت-بروكديل | CareGivers ISRAEL הארגון הישראלי לבני משפחה מטפלים

# የኮሮና ክትባት

ጥያቄ

**በተጣሉት የገደብ ቀናት  ውስጥ ክትባቱን መቀበል ይቻላል ?**

መልስ

ክትባትን ለመቀበልና በተለያዩ የሕክምና እንክብካቤዎችን  ለመቀበል ከሆነ ከምንኖርበት ቤታች ከ 1000 ሜትር በላይ መውጣት ይቻላል ፤

ይህ የኮሮና በሽታ መከላከያ ክትባት እናንተንና ተወዳጅ ቤተሰቦቻችሁን በበሽታው እንዳይጠቁ የሚረዳ በጣም አስፈላጊ  ዘዴ ነው ። በአሁኑ ጊዜ  በጣም አደኛ ደረጃ ላይ ያሉና ከ 60 ዓመት በላይ ያሉ አዛውንቶች ይህን ክትባት ይሰጣቸው ተብለው የተመረጡ የሕብረተሰቡ ቀዳሚ አካላት ናቸው ። ይህ የመረጣ ሂደት አንዳንድ ጊዜ እንዳስፈላጊነቱ የሚያስተካክለው የጤና ጥበቃ መ/ቤት ነው ፤ የትኞቹ የመሐበረሱ አካልት በቅድሚያ ክትባቱ መቀበል እንዳለባቸው የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ በጤና ጥበቃ የኢንተርኔት ድረ-ገጽ ላይ መመልከት ይችላሉ ፤

ይህ ክትባት የሚሰጠው በሕክምና ተቋሞች (ኩፓት ሆሊም) አማካኝነት አስቀድሞ  ተራ በማያዝ ነው ፤ ስለ ክትባቱ ተጨማሪ ማብራሪያ መቀበል ካስፈለገ ደግሞ ለሕክምናው ተቋም የመረጃ መቀበያ ማዕከል በመደወል ወይም ወደ ጤና ጥበቃ መ/ቤት የኢንተርኔት ድረ-ገጽ በመድረስ መረጃዎችን ማንበብ  ያስፈልጋል ፤

**የመረጃ መቀበያ ማዕከሎች ፤ ክላሊት ፤ *2700 ፤ መካቢ ፤ *3555 ፤ መኡሄዴት ፤ *3833 ፤ ሉሚት *507 ፤**

# በተጣለው የገደብ ጊዜ የቤተሰቦቻችን ጤንነት እንዴት መጠበቅ እንችላለን

ጥያቄ

**በተጣሉት የገደብ ቀናት ውስጥ ለውድ ቤተሰቦቻችንና ለሞግዚት ተንከባካቢ ሰራተኞች ዕርዳታ ማበርከት እንችላለንን ?**

መልስ

አዎ ፤ የተጣሉት የእንቅስቃሴ ገደብ የሚያስፈልገውን ዕርዳት ለመስጠት ከቦታ ወደ ቦታ በመሄድ ችግር ላይ ላለ ሰው የሚያስፈልገውን ዕርዳታ ማቅረብ የተጣለው ገደብ ይፈቅዳል ፤ ይህም የሕመምተኛውን ቤተሰቦችም ያጠቃልላል፡- ይህ ዓይነት ዕርዳታ ማበርከት በተጣለው የገደብ ቀናት ውስጥ እነዚህ ሰዎች ጊዜውን በጥሩ ሁኔታ እንዲያሳልፉ ይረዳቸዋል ፤ በአደገኛ ደረጃ ያሉትን የቤተሰብ አባላት ጤናቸውን ለመጠበቅ ሲባል የሚያስፈልገውን ዕርዳታ ስናበረክት የማህበራዊ እርቀትን በመጠበቅ ይሆናል ፤

ጥያቄ

**በተጣሉት የገደብ ቀናት ውስጥ ፤ የተለያዩ ሐኪሞችና ባለሙያዎችና ከቤታች በመምጣት ሊጎበኙን ይችላሉን ?**

መልስ

አዎ ፤ የሚያስፈልገውን የሕክምና እንክብካቤ ከሕመምተኛው ቤት በመሄድ መስጠት ይቻላል ፤ የሕክምና አገልግሎቱ የሚያበረክተው የሕክምና ባለሙያ የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ማድረግ የ 2 ሜትር እርቀትን መጠበቅ አለበት ፤

**ጥያቄ** **የቤተሰባችን አካል የሆነ አንድ አዛውንት ሕመም ቢያጋጥመው ምን ማድረግ አለብን ?**

**መልስ** ሁልጊዜም የተለመዱ ነገሮችን ማድረግ ያስፈልጋል ፤ አንድ ሰው ሕመም ከተሰማው ወደ ሐኪም ቀርቦ ማማከር ያስፈልጋል ፤ የቤተሰብ ሐኪማችን በስልክ ወይም ወደ ክሊኒኩ በመሄድ ማማከር ይቻላል ፤ እንዳንድ የሕክምና አገልግሎቶች ዛሬ የሚሰጡት በዕርቀት ነው፣ ስለዚህ አስፈላጊውን መረጃ ለመቀበል ወደ ሕክምና መረጃ የመቀበያ ማዕከሎች ማመልከት ይቻላል ፤

**ጥያቄ** **በተጣሉት የገደብ ቀናቶች ውስጥ ፤ ሁልጊዜ የምንቀበለውን የሕክምና አገልግሎት ምርመራዎችን ማድረግ እንችላለን ?**

**መልስ** አዎ ፤ አስፈላጊ የሆኑ የሕክምና አገልግሎቶችን ለመቀበል ማዘናጋት አያስፈልግም ፤ ወደ ሆስፒታል ወይም ወደ ሕክምና ተቋማት በመሄድ ሕክምናውን መቀበል ያስፈልጋል ፤

**ጥያቄ** **እናቴ የመድኃኒት መግዣ ማዛዣ ደብዳቤ መቀበልና መድኃኒቱም ገዝታ ማምጣት ትፈልጋለች ፤ ሆኖም ይህን ማድረግ አትችልም ፤ ስለዚህ ምን ማድረግ ይቻላል ?**

**መልስ** ብዙዎችን የመድኃኒት መግዣ የትዕዛዝ ደብዳቤዎች ፤ ሕክምና ከሚያበረክትልን ሐኪም በስልክ ወይም በኢንተርኔት ድረ ገጾች ማዘዝ ይቻላል ፤ ወደ ሕክምና ተቋሞችና ወደ መድኃኒት መግዣ ፋርማሲዎች መምጣት የማይችሉ ሕሙምተኞች ወደ ሕክምናው ተቋም የመረጃ መቀበያ ማዕከል በመደወል አስፈላጊውን መረጃ መቀበል ይቻላል ፤

**የመረጃ መቀበያ ማዕከሎች ፤ ክላሊት ፤ *2700 ፤ መካቢ ፤ *3555 ፤ መኡሄዴት ፤ *3833 ፤ ሉሚት *507 ፤**

**ጥያቄ** **በአዛውንቶች መንከባከቢያ ድርጅቶች የታመሙ አዛውንቶችን አስተኝቶ እንክብካቤ መስጠት ጀምረናል፣ይህም የሚያስፈልገውን ግንኙነት ከጤና ጥበቃ መ/ቤት ጋር በመፍጠር ነው ፤ የሚሰጡት እንክብካቤዎች በተጣለው የገደብ ቀናት ውስጥ የሚቀጥሉ ከሆነ ፤ ወደ ማን ማመልከት ይቻላል ?**

**መልስ** አዎ ፤ የጤና ጥበቃ መ/ቤት ሠራተኞች ሥራቸውን መሥራት ቀጥለዋል ፤ ስለዚህ የሕክምናው ሂደት በምን ደረጃ እንደደረሰ መመርመር ይችላሉ ፤ የሚያስፈልገውን የእንክብኬ ሁኔታ ለመርዳት ፤ በያላችሁበት አካባቢ ወደ አዛውንቶች ለማህበራዊ ሠራተኛ ማመልከት ትችላላችሁ ፤ የእነዚህን የጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤቶች ቢሮ ዝርዝር መረጃ ለማንኘት ወደ ጤና ጥበቃ የኢንተርኔት ድረ-ገጾች ይጎብኙ ፤

# ከቢጡዋህ ሉሚ ስለሚሰጥ ድጎማ

ጥያቄ

**በተጣሉት የገደብ ቀናት ውስጥ ፤ እንክብካቤ የሚሰጡ ሞግዚቶች ላይ የተለየ የሥራ መቀየር ይኖራልን ?**

መልስ

በአጠቃላይ በገደቡ ቀናት ውስጥ ምንም የተቀየረ ነገር የለም ፤ እንክብካቤ የሚያበረክቱ ድርጅቶች ሥራቸውን እንደተለመደው ይቀጥላሉ ፤ እንክብካቤ ተቀባቶች ደግሞ የጤና ጥበቃ መ/ቤት የሰጠውን የጥንቃቄ መመሪያ ማድረግ አለባቸው ፤ ከዚህ ባለፈ ግን ፤ እንክብካቤ የሚያደርገው የሞግዚት ሠራተኛ ወደ ሥራው ካልመጣ ፤ ከድርጅቱ ጋር በመነጋገር ተቀያሪ ሠራተኛ እንዲላክ ማድረግ ያስፈልጋል ፤

ጥያቄ

**አባቴ ፤ በአዛውንቶች መሰባሰቢያ ማዓከል አንዳንዴ ጉብኝት ያደርጋል ፤ በዚህ ሁኔታስ የተቀየረ ነገር አለን ?**

መልስ

የማህበራዊ አገልግሎትን በተመክለከተ ኃላፊነት ያለው መ/ቤትና የሥራ መ/ቤት በሰጡት መመሪያ መሰረት ፤ የአዛውንቶች መሰባሰቢያ ማዕከሎች ስይዘጉ ክፍት ይሆናሉ ፤ በማዕከሉ ለውጥ ካለ ወይም አዛውንቱ ከቤቱ መሆኑን የሚፈልግ ከሆነ የሚያስፈልገውን ዕርዳታ ከቤቱ ሆኖ መቀበል ይችላልን ፤ ይህን አገልግሎት ለመቀበልም ፤ ወደ ድርጅቱ (እንክብካቤውን የሚያበረክተው) በስልክ ግንኙነት መፍጠር ያስፈልጋል ወይም ደግሞ ለአዛውንቶች በቅያሪ የሚሰጡ እንክብካቤዎች ማዕከል ማመልከትም ይቻላል ፤

ጥያቄ

**በዚህ ወቅት እናቴ ወደ ሌላ አገር በመሄድ ከዘመድ ተጠግታ መቆየትን መረጠች ፤ ይህን እንክብካቤ እናቴን በሚያስተናግዳት ቤት ዘመድ ቤት ውስጥ መቀበል ትችላለች ?**

መልስ

አገልግሎቱን መቀበል ይቻላል ፤ ለዚህም ወደ ቢጥዋህ ሉሚ የአቅመ ደካሞች መርጃ አገልግሎት ማዕከል በስልክ ***2637** መደወል አለብን ፤ እንክብካቤውን ከሚያበረክተው ድርጅት ጋር በመነጋገርም እንክብካቤው የሚሰጥበትን አድራሻ መቀየር ያስፈልጋል ፤ ወደ ሌላ ቦታ በመቀየራችን ሰበብ አገልግሎት የሚሰጠውን ድርጅትም መቀየር የሚያስፈልግ ከሆነ መቀየር ይቻላል ፤ አቅመ ደካማው በማህበራዊ ጉዳይ መ/ቤት አማካኝነት በሚኖርበት ከተማ ውስጥ ገንዘብ በመክፈል ወይም በበጎ ፈቃደኛ ሠራተኞች በኩል አገልግሎቱን የሚቀበል ከሆነ ፤ አድራሻችንን ስለመቀየራችን ለማህበራዊ ሠራተኛና መ/ቤት  ማሳወቅ ያስፈልጋል ፤ በተጨማሪም ፤ በገድቡ ቀናቶች ለትንሽ ጊዜ ቤታችንን መቀየራችንን ለጎረበት ማሳወቅ አለብን ፤

**ጥያቄ**

**በገደቡ ቀናት ውስጥ ለወላጆች የቢጥዋህ ሉሚ ማህበራዊ ሠራተኛ መጥታ እንድትጎበኛቸው ተራ ተይዞላቸዋል ፤ የተያዘላቸው የጉብኝት ቀጠሩ ይሰረዛል ? የሚሰጡት እንክብካቤስ እንዴት ይሆናል ?**

**መልስ**

በአጠቃላይ ፤ የቢጥዋህ ሉሚ ማህበራዊ ሠራተኞች የቤት ጉብኝት አያደርጉም ፤ ገደቡ ከመጣሉ በፊት የተመዘገቡ ሥራዎች የቤት ጉብኝት ሳያደርጉ መልሱን ይሰጣሉ ፤ የገደቡ ቀናቶች ካበቁ በኋላ አስቀድሞ ተራ በመያዝ ሠራቸውን እንደገና መሠራቱን ይቀጥላሉ ፤

**ጥያቄ**

**በኮሮና በሽታ ምክንያት የእንክብካቤ ሠራተኛ / ሞግዚት ከቤታችን ልናስገባ እንፈራለንን ስለዚህ ያለን የእንክብካቤ መብት ምን ሊሆን ይችላል ?**

**መልስ**

የእንክብካቤ መቀበል መብት ያለው አዛውንት እንክንካቤ የሚያደርግለት ሞግዚት / ሠራተኛ በኮሮና በሽታ ምክንያት ከቤቱ አላስገባም ካለ እንክብካቤው በገንዘብ ተቀይሮ እስከ ሜርጽ 2021 ዓ.ም መቀበል ይችላል ፤

**ጥያቄ**

**አንድ አዛውንት ያለበት ሁኔታ በጣም እየከፋ ከመጣና ስለ እንክብካቤ ለመቀበል የሚያስፈልጉትን የማመልከቻ ሰነዶች በገደቡ ቀናት ማመልከት ይቻላል ?**

**መልስ**

በገደቡ ቀናት ማመልከቻዎችን በኢንተርኔት በኩል ወይም በቢቱዋህ ሉሜ ፖስታ ፤ በፋክስ በመላክ አማካኝነት ማመልከቻዎችን ማቅረብ ይቻላል ፤ እነዚህ ማመልከቻዎች በእንክብካቤ ሰጭ ሠራተኞች በኩል የሚያስፈልገው ክትትል ይደረግለታል ፤ ለተጨማሪ መረጃዎች ወደ ቢጥዋህ ሉሜ የኢንተርኔት ድረ ገጽ መጎብኘት ይቻላል ፤

# በገደቡ ቀናት ፤ የእስራኤላዊ ዜግነት የሌላቸውን ሠራተኞች ስለማሠራት

ጥያቄ

**በገደቡ ቀናት ውስጥ የእስራኤል ዜግነት ስለሌላቸው ሠራተኞች የተሰጡት መመሪያዎች ምን ምን ናቸው ?**

መልስ

እንደማንኛውም ዜጋ ፤ እነዚህ የገደብ ቀናት የእስራኤላዊ ዜግነት በሌላቸው ሠራተኞች ላይም ሥራ ይውላሉ ፤ ከዚህ በታች እስራኤላዊያን ስላልሆኑ ሠራተኞች የመመሪያ ጦማር በዝርዝር ይቀርባሉ ፤ በዜጎችና በሕዝብ ብዛት በኩል የሚሠራው መ/ቤት ድረ ገጽ ላይ በተለያዩ ቋንቋዎችም ሊያገኙ ይችላሉ ፤

ጥያቄ

**በገደቡ ቀናት ውስጥ ይህ የእስራኤል ዜግነት የሌለው ሠራተኛ ከእንክብካቤ ተቀባዩ ቤት የዕረፍት ቀናትን በመጨመር መቀመጥ አለበትን ? ለዚህ ተጨማሪ ክፍያስ ያስፈልገዋልን ?**

መልስ

ማንኛውም የእስራኤል ዜግነት የሌለውና በተለያዩ ድርጅቶች አማካኝነት እንክብካቤ እያበረከተ የሚሠራ ግለሰብ ፤ በህጉ መሰረት ሰባተኛው ቀን የዕረፍት ቀን መሆን አለበት ፤ በተጣለው ገደብ ይህ ሠራተኛ ከእንክብካቤ ተቀባዩ ቤት መቀመጥ ካለበት ፤ በዚህ ቀን ሥራ ከመሥራት ነፃ ይሆናል ፤ ይህ ሠራተኛ በዚህ ቀን ሥራ ስለማይሠራ ተጨማሪ የሥራ ቀን ነው ብሎ መሰየም አይቻላም። ስለዚህ ተጨማሪ ክፍያ መክፈል አያስፈልግም ፤ አንድ ሠራተኛ በዕረፍት ቀኖች ላይ የጤና ጥበቃ መ/ቤት የሰጠውን መመሪያ በመከተል መውጣት ይችላል ፤

ጥያቄ

**የእስራኤል ዜግነት የሌለው የእንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢ ሠራተኛ ለመቀበል ምን ማድረግ አለብን ? ሥራ የሌላቸው ሠራተኞችስ እንዴት ማግኘት ይቻላል ? ከውጭ አገር የውጭ ሠራተኛ ማስመጣት ይቻላል ?**

መልስ

የሞግዚት የሥራ ፈቃድ ለመቀበል በ 99 የድርጅቱ ቅርንጫፎች - የግል ጽህፈት ቤቶች ወይም የሥራ ፈቃድ በሚሰጠው የእንክብካቤ አበርካች ድርጅት አማካኝነት ከበታው በመሄድ ወይም በፖስታ አማካኝነት ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል ፤ ቅርንጫፎች የሚገኙበት ቢታዎችም ፤ እየሩሳሌም ፤ ቤኤር ሸቫ ፤ ሀይፋ ፤ ቴል አቪቭ ፤ ክፋር ሳባ ፤ ሪሾን ለጺዮን ፤ እነዚህ የድርጅቱ ቅርንጫፎች በተጣሉት የገደብ ቀናትም ሥራቸውን መሥራት ይቀጥላሉ ፤ በኢንተርኔት አማካኝነት ለተላኩ የማመልከቻ ደብዳቤዎች በድርጅቱ የኢንተርኔት ድረ ገጽ አማካኝነት ክትትል ማድረግ ይቻላል ፤ ፈቃዱን ከተቀበልን በኋላ ሥራ የሌለውን የሞግዚት ሠራተኛ ለማግኘት ሕጉን በመጠበቅ ሠራተኛውን ለሚፈልገው የመንግሥት ድርጅት ማመልከት ያስፈልጋል ፤ ይህም ድርጅት 99 ቅርንጫፎች አሉት ፤ በተጨማሪም ፤ በግል የሥራ አፈላላጊ ድርጅት ማመልከት ያስፈልጋል ፤ ከውጭ አገር ሠራተኞችን ለማስመጣት ደግሞ ፤ የተጣለውን ገደብና መመሪያዎች በመመርኮዝ የሚያስፈልገውን የማመልከቻ ደብዳቤ ማቅረብ ያስፈልጋል ፤

**ጥያቄ**

**የሞግዚቱ/ ሠራተኛው በገደቡ ቀናት ውስጥ የሥራ ፈቃዱ ጊዜ ካበቃ ምን ማድረግ አለብን ?**

**መልስ**

የውጭ አገር ሠራተኞች ጉዳይ ተከታታይ ድርጅት «መ/ቤት» አማካኝነት የሥራ ፈቃዱ እንዲራዘም ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል ፤ ይህ ድርጅት በተጣሉት የገደብ ቀኖች ውስጥም ሥራውን መሥራቱን በመቀጠል የሚያስፈልጉትን ፤ የመሥራት ፈቃድ ያላቸውን መ/ቤቶ ዝርዝርና ያሉበትን ቦታዎች ለማወቅ ወደ ኢንተርኔት ድረ ገጹ መጎብኘት ያስፈልጋል ፤

- የሞግዚቱ / ሠራተኛው ሁኔታ የት እንደደረሰ ያሚያመላክት የመገናኛ ምልክት ፤
- የሥራ ፈቃድ ደብዳቤው ጥያቄ ውሳኔ የት ደረጃ እንደደረሰ ለማወቅ ፤

**ጥያቄ**

**ለአያቴ እንክብካቤ የሚያደርግላት የሞግዚት / ሠራተኛ ለኮሮና በሽተኛ ጋር ግንኙንት ማድረጉ ቢታዎቅ ወይም የኮሮና ሕመምተኛ ቢሆን ምን ማድረግ እችላለሁ ? (ለማን ማመልከት ይቻላል ፤ የመገለያ ቦታ ለመስጠት ኃላፊነት ያለው ማን ነው ፤ ሠራተኛውን የሚተካ ሌላ ሠራተኛስ እንዴት ማግኘት ይቻላል ?)**

**መልስ**

የሞግዚት ሰራተኞች ኃላፊ ቢሮ የሞግዚቶች / ሠራተኞች የሚቀጥሩ ሰዎችን ለሠራተኛው አስፈላጊውን የድህንነት ዋስትና እንዲያደርግ ያስገድዳል ፤ ሠራተኛው / አሠሪው ወደ ሐክምና ተቋሙ በመደወል ምን ማድረግ እንዳለበት አስፈላጊውን መመሪያ መቀበል ይኖርበታል። አንድ ሠራተኛ በኮሮና የታመመ ከሆነ የጤና ጥበቃ መ/ቤትና የሕክምናው ተቋም በሚሰጡት ፈቃድ መሰረት ወደ መገለያ ቦታ ማለትም ወደ ትንንሽ ሆቴሎች ይላካል ፤

ቀያሪ ሠራተኛ ስለማግኘት - ቀያሪ ሠራተኛን ለማምጣት የሚረዳውን የግል ድርጅት ማማከር ያስፈላጋል ፤

## እንክብካቤ የሚቀበለው ግለሰብ ቤተሰቦችን ስለመርዳት ፤

**ጥያቄ**

**በዚህ የኮሮና ወረርሽኝ በሽታ ወቅት በጣም ስለምወዷቸው የቤተሰቤ አባላት ሁኔታ በጣም ውስብስብና ከባድ የሆነ ስሜቶች ይሰማናል ፤ ስለዚህ ጉዳይ ከማን ጋር መወያየት ይቻላል ?**

**መልስ**

እንደ እንክብካቤ ተቀባይ ቤተሰብ ፤ በዚህ ጊዜ መመካከርና መረዳዳት በጣም አስፈላጊ ነው ፤ ለአንተ የሚያስፈልገውን ዕርዳታና ምክር የሚሰጡ ብዙ ተቋሞች አሉ። ስለዚህ ወደ እነዚህ ተቋሞች በማመልከት የሚያስፈልገው ምክርና ደጋፍ መቀበል ትችላለህ ፤ የግንኙነት መፍጠሪያ መንገዶችን ወደ መጨረሻው አካባቢ ይዘረዘራሉ ፤

## ስለነዚህ ጥያቄዎች ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት ፤ ለተጨማሪ ጥያቄዎችና ዕርዳታዎች ፤

- ኮል ሃብሪኡት ፤ የጤና ጥበቃ የስልክ ደጋፍ አበርካች - ***5400**
- አቅመ ደካማ የሆኑ ሰዎችን የሚረዳ የቢጥዋህ ሉሚ ማዕከል - ***2637**
- የሥራ ኃላፊ ፤ የማህበራዊ ጉዳይና የማህበረሰብ ነክ የሆኑ ጉዳዮች ተከታታይ መ/ቤት - **118**
- **በቤተሰባቸው ውስጥ አቅመ ደካማ የሆኑ ቤተሰቦቻቸውን እንክብካቤ ለሚያበረከቱ የሚሰጥ የሕብረተሰባዊ መ/ቤት ድጋፍ** ፤
- የማሕበረሰብ የእኩልነት መ/ቤት የመረጃ ማዕከል - ***8840**
- የስደተኞችና የዜጎች መከታተያ መ/ቤት - የምክርና የድጋፍ ሰጭ ማዕከለ - ***3450**
- ስለሞግዚት ሠራተኛ በስልክ የሚሰጥ የድጋፍ መረጃ ማዕከል - ቀጣይ የኋላፊነት ሁኔታ - ***6107**
- **ለሞግዚት ሠራተኛ የተሰጡ መመሪያዎች** ፤
- የደጀን ወታደሮች የመረጃ መእከል - **104**
- የከተማ መረጃ መቀበያ መዕከል - **106**
- **የጆይንት እስራኤል የኢንተርኔት ድረ ገጽ**

## ቤተሰብን ለሚንከባከቡ የሕብረተሰቡ አካላት የሚሰጥ የድጋፍና የዕርዳታ ማዕከል ፤

- የድጋፍና የዕርዳታ ማዕከል Caregivers እስራኤል - WhatsApp (በዋትስ አፕ) የሚደረግ የጥያቄና መልስ መስጫ ስልክ ቁጥር - **055-9993311**
- በቢጥዋህ ሉሚ ያማካኝነት ለአቅመ ደካማ አዛውንቶችና ቤተሰቦቻቸው የመረጃ መቀበያ ማዕከል - ***9696**
- ኤዜር ሚጺዮን - እንክብካቤ ለሚያቀርቡ ቤተሰቦች የምክርና ዕርዳታ መስጫ ማዕከል - **1-800-80-20-30**
- ኤምዳ - በቤተሰባቸው ውስጥ በዲሜንጺያ / አልጽሃይመር በሽታ ለሚሰቃዩ ሰዎች የመረጃ መቀበያ ማዕከል - ***8889**
- በቤተሰባቸው የአልጽሃይመር በሽተኞችና ለቤተሰቦቻቸው የመርጃ ማዕከል - ለ **24/7** ሰዓታት የሚሰራ **079-5801111**
- ናታል - በኮሮና በሽታ አማካኝነት ለሚደርሱ ፍርሃቶች ምክር መስጫ ማዕከል - **073-2363380**
- የሚረዳ እጅ - በያድ ሳራ አማካኝነት ዕርዳታ ለሚያገኙ ቤተሰቦች የመረጃ መቀበያ ማዕከል - **02-6444678**
- ረኡት - በአዛውንቶች ዙሪያ ስለሚሰጡ እንክብካቤዎች ጉዳይ መረጃ መቀበያ ማዕከል - **1-700-700-204**